# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 19

ግንቦት 21 ቀን 2014 ዓም (29-05-2022)

ባለፉት ጊዜያቶች ባቀረብናቸው ተከታታይ ዘገባዎቻችን ያገራችን የለት ዕለት ጉዞ ከድጡ ወደማጡ እንደሆነ ያሳዬንበት እንደነበር ይታወሳል፤የአሁኑም ዘገባችን በከፋ ደረጃ ፣በጣር ላይ መሆኗን የሚያሳይ እንጂ የተሻላት መሆኑን የሚያመለክት አይደለም።ይህንን ስንገልጽ ለመጻፍም እዬከበደንና እያስጨነቀን ነው።የመንግሥት ነኝ ባዩ ቡድን የሚፈጽመው በደልና አገር የማፍረስ ሴራ በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ ሲካሄድ ፣ለዚህ ተግባር አጋዥ ሃይል ሆኖ የሚሰለፈውን የአማራውን ሆድ አደር ስናይ ልባችን ይደማል፣ስሜታችን ይነካል።ነገር ግን ሌላ ምርጫ ስለሌለን በጀመርነው የትግል ዘርፍ ይበልጥ ተጠናክረን እንድንቀጥልበት ያስገድደናል እንጂ ተስፋ ቆርጠን እጃችንን እንድንሰጥ ወይም ከትግሉ ቦታ እንድናፈገፍግ አያደርገንም።ለነጻነትና ለእኩልነት በተለይም ለአገር ልዑላዊነት የሚከፈለው ውድ የህይወት ዋጋ መኖሩን እንገነዘባለን።ካለትግል ብሎም ካለመስዋእትነት የሚገኝ ክብርና ነጻ አገር ስለማይኖር ለዚያ ግዳጅ የምንችለውን ለማበርከት የመከራው ስፋትና ጥልቀት ይቀሰቅሰናል፣እልህ ውስጥ እንድንገባ ያደርገናል እንጂ ሸብረክ እንድንል አያደርገንም።

ከዚህ አቋም ስንነሳ እኛ ብቻ ሳንሆን በዱር በገደል እምቢ ላገሬ ለነጻነቴ ብለው የህይወት ዋጋ ለመክፈል የተሰለፉ መኖራቸውን ስናይ የልብ ልብና የሞራል ጥንካሬ ይሰጠናል።እነሱ በጋለ ምጣድ ላይ ሆነው ሞትን ሳይፈሩ፤ቤተሰብ፤ትዳርና ጎጆ፣ልጅና ሃብት ሳያጓጓቸው ከቤታቸው ወጥተው በዱር በገደሉ ሲዋደቁ እያዬንና እዬሰማን በተዝናና አገርና ኑሮ ውስጥ እያለን የነሱን 1% የሚሆን ተሳትፎ አለማድረግ ከሰውነት ደረጃ የሚያወጣና ከአውሬ ደረጃ የሚያሰልፈን ይሆናል።ጥቂቶቹ የእኩይ ስርዓት ደጋፊዎች ተባብረው አገር ሲያጠፉ እኛ በቁጥርም ሆነ በንቃተ ህሊና እንዲሁም በአቅምና የዓላማ ብልጫ የምንሻለው ሳንደራጅና ሳንሰባሰብ መቅረታችን በራሳችን ላይ የሚሰነዘር ዱላ ለአጥቂው ሃይል እንደ ማቀበል ያህል ይቆጠራል።ምን ጊዜም የጸረ ሕዝብ ሃይሎች ጉልበት የሚበረታው ሕዝባዊ ሃይሉ ከተዳከመና ከተዝረከረከ ብቻ ነው።

በስልጣን ላይ ያለው የኦሮሙማው ተረኛ ቡድን ለምንና ለማን እንደቆመ ምስጢር የሆነበት ቢኖር እንደሰው ለማዬትና ለማሰብ ያልቻለ ድኩማን ወይም ጥቅምና ፍርሃት ያወረው ብቻ ነው።በኢትዮጵያ መሬት ላይ ምን እንደሚካሄድ ለማወቅ የግድ ኢትዮጵያዊ መሆንና ወይም በዚያው መኖር አይጠይቅም።ለህሊናው ያደረና የዓለም ፖለቲካ ብሎም የሰው ልጆች ስቃይ የሚያሳስበውና የሚከታተል ሁሉ በገሃድ የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ስለሆነም ስለኢትዮጵያ የሚያስቡና የሚጨነቁ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳንሆን አያሌ የሌላ አገር ዜጎች ጭምር ናቸው።በኢትዮጵያ ውስጥ የሰፈነው የጎሳ ፖለቲካና ያመጣው መዘዝ ወደ አገራቸው እንዳይገባ በመንግሥታዊ ተቋማትና ብሎም በጸሎት የሚከላከሉ ሕዝብና አገሮች ብዙ ናቸው።ኢትዮጵያ የረሃብ፣የስደት፣የግጭት፣የሁሉም አይነት አስፈሪ ገጾች ምሳሌ ከሆነች ውሎ አድሯል።ይህንንም አስፈሪ ገጽ ያላበሳት በጎሳ መብት ሰበብ እንድትፈራርስ መሣሪያ አንግቦ ንጹሃን ዜጎችን የሚገል ፣የሚዘርፍ ለባእዳን ያደረ ከአብራኳ የወጣ የራሷ ልጅ ነው። ይህ አጥፊ ቡድን እዬተቀያዬረ በተረኝነት የሥልጣን እርከቡን ከተቆጣጠረበት ከዛሬ 31 ዓመት ጀምሮ የሚፈጽመው ወንጀል በአይነትም በጭካኔም ይበልጥ እያደገ እንጂ እዬቀነሰ አልመጣም።ለዚያም ነው ግፍና በደሉ ያስመረረው አገር ወዳድና የሰብአዊ መብት ታጋይ በቃኝ ብሎ ለመፋለም ወስኖ ትግሉን የጀመረው።

የአብይ አህመድ መንግሥት ለአገራቸው አንድነትና ለፍትህ መስፈን ሲሉ ለትግል የተሰለፉትን ሃይሎች ኢመደበኛና አሸባሪ በማለት ፈርጆ በመግደልና በማፈን ላይ ተሰማርቷል። የአገር መከላከያ ጦሩን ከተት ያለው የወያኔና የኦነግ ጥምር ቡድን ላላቸው አገር የማፍረስ ዓላማ እንቅፋት የሆነውን የአማራውን ማህበረሰብ ለማጥፋት የነደፉትን የረጅም ጊዜ እቅድ ለመተግበር ከመቼውም ጊዜ በተለዬ መልኩና ሁለገብ ዝግጅት ፣የሸዋን ፣የጎጃምን፣የጎንደርንና የወሎን ክፍላተሃገር ዙሪያ ከበባ በማድረግ እንደ ውጭ ጠላት በጭካኔ ንጹሃንን በመጨፍጨፍ ላይ ናቸው።በተለይም ከአማራው አብራክ የወጡትን ነፍጥ ያነሱትን አገር ወዳዶችና የሙብት አርበኞች ፋኖዎችን ለማጥፋት በሁሉም ዘርፍ ጦሩን አሰልፎ የሽብር እርምጃ በማካሄድ ላይ ነው።በዚህ ጭፍን እርምጃ የሚሞተው መሣሪያ ታጥቆ በዱር በገደል የሚፋለመው ፋኖ ብቻ ሳይሆን አንድ የ13ዓመት ዕድሜ ያለው ታዳጊ ሳይቀር በጥይት ተደብድቦ ሞቷል።ከከባቢው ኑዋሪ ጋር በቋንቋ የማይግባባ፣ለሰው የማይራራ ጨካኝ የመንግሥት ጦር ልጅ አዋቂ ሳይል ያገኘውን እያጨደ ነው።

አማራ የሚል መለያ የሰፈረበትን የመታወቂያ ወረቀት የያዘ ሰላማዊ ዜጋም ከእስራትና ከእንግልት አላመለጠም።ሲጀመርም በዜጎች መታወቂያ ወረቀት ላይ የጎሳ ማንነት ማስፈሩ ጤነኛ አለመሆኑን ለዚህ አይነቱ ጥቃት እንደሚዳርግ ቀድመው ያወቁና የተቃወሙ መኖራቸው አይካድም።ዜጋ በአገራዊ ዜግነቱ እንጂ በጎሳው ማንነት የሚታወቅበት ምንም አይነት ዓለም አቀፋዊ ሕግና የፍትሕ መሠረት የለም።ግፋ ቢል የሥራ መታወቂያ ላይ የሚገለጽ የሙያ ስም ይኖራል።በናዚዎች ዘመን አይሁዶችን ለመለዬትና ለማጥፋት ሲባል በደረታቸው ላይ የሚለጠፍ ምልክት የተደረገ ግዳጅ እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል። በአፍሪካዋ ሮዋንዳም ቤልጅጎች ወረው በያዙበት ጊዜ ሕዝቡን ሁቱና ቱትሲ በማለት በጎሳ ለያይተው መታወቂያ ማደላቸው የሚታወቅ ነው። ይህንን የወራሪዎች መሰሪ ዓላማ ተከትሎ ሩዋንዳ ከቤልጅጎች ነጻ ስትሆን የቀበሩት የጎሳ ቦምብ ለ1994ቱ በዓለማችን ወደር ለሌለው የእርስበርስ እልቂትና ጎሳ ተኮር ጭፍጨፋ ዳርጓቸዋል።ይህም ለሩዋንዳውያን ትልቅ የታሪክ ጠባሳና የሃፍረት ማህተም ያሸከመ ነው።

በኢትዮጵያም የሰፈነው የጎሰኞች ስርዓትና ፖለቲካ ሕዝቡን በጎሳ ሸንሽኖ፣ክልል በሚል በረት ውስጥ አምቆ እርስ በርሱ እንዲባላ የማድረጉ ሴራ ናዚዎችና ቤልጅጎች ከፈጸሙት የዘር ማጥፋት ወንጀል ቢበልጥ እንጂ የሚተናነስ አይደለም።የሚበልጥበትም ምክንያት በሁለትና በሦስት ጎሳዎች መካከል ብቻ ሳይሆን ከሰማንያ በላይ በሆኑ ጎሳዎች መካከል የሚፈጠር ግጭትና ጦርነት የሚያስነሳ በመሆኑ ነው። የኦሮሙማውና የወያኔው ጥምር ቡድን ጠላቴ ነው ከሚለው ጎሳ ፣ከአማራው ተወላጅ ውጭ ለሚፈጽመው የወንጀል ተግባር የማይተባበሩ የራሱ ጎሳ ተወላጅ የሆኑት ጭምር የጥቃቱ ሰለባ ሆነዋል። በሥርዓቱ ላይ ትችት የሚሰጡ፣በጥቅምና በማስፈራራት ያልተበገሩ ጋዜጠኞች፣የማህበረሰብ አንቂዎች ላይ የሚደርሰው አፈናና ማሳደድም የዚሁ የመንግሥት የሽብር አካል ነው።ከጠመንጃ ይልቅ ብዕር የሚፈራው የጅሎችና የሌቦች ጥርቅም መንግሥት ነኝ ባይ ቡድን በሃሳብ ሊረታቸው ያልቻለውን በማሰርና በመግደል ሃሳባቸውን የቀጨና ያሸነፈ ስለሚመስለው የእውር ድንብር ጉዞውን ቀጥሎበታል። ብዙዎቹ በመሳደድ ላይ ናቸው።አሉ የሚባሉ የፖለቲካ ተንታኞች፣ተችዎችና የማህበረሰብ አንቂዎች፣ ጋዜጠኞችና የተቃዋሚ ድርጅት አባላት ሳይቀሩ በነቂስ ተለቅመው ወደ እስር ቤት ተወርውረዋል። ስማቸውን ለመዘርዘር አፈናው ገና በሂደት ላይ ስለሆነና ሁሉንም ስለማያካትት ለጊዜው ከመጥቀስ ተቆጥበናል።የፖለቲከኞችና የጋዜጠኞች በገፍ መታሰር እስር ቤቱን የፖለቲካ መድረክ አድርጎት ምናልባትም “አብዮቱ እስር ቤት ውስጥ ተነሳ / ተጀመረ”! የሚል ዘገባ የምናሰማበት አጋጣሚ ሊሆን ይችላል።ፖሊስ አካላቸውን እንጂ ትግላቸውን አያግተውም።

የትግሉ ወርድና ስፋት እየጨመረ፣የሕዝቡ እምቢባይነት እያደገ ሲመጣ በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ከዓላማ አጋሩ ከወያኔ ጋር በምክክርም፣በንግግርም ስውር ግንባር ፈጥሮ፣ በመካከሉ ያለውን የስልጣን

ሸኩቻና ቅራኔ አሶግዶ በጋራ ጠላታቸው በሆነው በኢትዮጵያዊነትና በተለይም በአማራው ላይ የከተት ዘመቻ ማወጃቸው የሚገርም አይሆንም።ፋኖን ብቻም ሳይሆን የፋኖ ቤተሰብ፣ጓደኛና ጎረቤት ሳይቀር እዬተቀፈደደ መከራ በማዬት ላይ ነው።በዚህ ዓይን ያወጣ የጭካኔ እርምጃ የሦስት ዓመት ልጅ ሳይቀር በተሰወረው ፋኖ አባቱ ምክንያት ከቤተሰቡ ተነጥሎ ታፍኖ ለስድስት ቀናት በእስርቤት መቆዬቱ የዓለምን ሕዝብ ያነጋገረና ስርዓቱን ያጋለጠ ድርጊት ነው።ልጅም ብቻ ሳይሆን እንስሳትም በእግት ተይዟል።አንድ ውሻ በአህያ እያመላለሰ የሚሸጥ ደሃ ለፍቶ አደር ለፋኖ ይሰልላል፣ምስጢር ያደርሳል ተብሎ እጁን ለፖሊስ እንዲሰጥ ቢጠዬቅ እምቢ ብሎ በመሰወሩ የነበረችውን የመተዳደሪያውን አንድ አህያ አፍነው መውሰዳቸው በቦታው ለሚኖረው ነዋሪ መነጋገሪያ ሆኗል። እጁን ለመያዝ ወይም ለመግደል ያልቻሉት የፋኖ መሪ ወላጆች የሚኖሩበት ቤት በፈንጅና በከባድ መሣሪያ ተደብድቧል። መነኩሴ እናትም ተንገላተዋል።

ተረኛው የኦሕዴድ ብልጽግና አገር አጥፊ የሌቦች ቡድን የኢትዮጵያን ድንበር አልፋ መሬት በወረረችው ሱዳን ወይም ኦነግ ሸኔ ብሎ በሚያጭበረብርበት የራሱ ታጣቂ ላይ ያልሞከረውን የድሮን ዘመቻ በአማራው አገር ወዳድ ላይ ማሰማራቱ ምን ያህል ጨካኝና ከሃዲ መንግሥት እንደሆነ ማሳያ ነው። አሁን በአማራው ላይ ያሰማራው የጦር ሃይል ብዛቱና የመሣሪያው አይነት ለውጭ ወራሪ ከሚያሰልፉት ሃይል ቢበልጥ እንጂ አያንስም።ይህንን የጥፋት ዘመቻ ሕግ የማስከበር የሚል ስያሜ ቢሰጡትም በትክክለኛው መጠሪያና መመዘኛ ግን ሥልጣን ማስከበሪያ ነው ማለቱ ትክክለኛ ነው።ይህንን የመንግሥት ዘመቻ በመደገፍ በርታ! በለው ! የሚሉ ሆድ አደር ጋዜጠኞች፣ምሁራን፣የሃይማኖት መሪዎች...ወዘተ እንዳሉ ሁሉ የሚያወግዙና የሚቃወሙ ምሁራን፣የእምነት አባቶች፣የኪነት ሰዎች፣ ጋዜጠኞች፣ነጋዴዎች መኖራቸው ለሥርዓቱ ውጋት ሆኖበታል፤በእነሱም ላይ የማጥቃት እርምጃውን ከመውሰድና ከማስፈራራት አልታቀበም።በየተራ እዬለቀመ በማሰር ላይ ነው።ዛሬ ያልታሰረ የነገ እስረኛ ላለመሆኑ ዋስትና የለም።ይህ ሁሉ ታዲያ ወዴት ያመራል?

ባለፉት ጊዜያቶች ደጋግመን እንዳልነው ዛሬም የምንለው ግፍና መከራው በጨመረ ቁጥር የነጻነትና የዴሞክራሲው ትግል እያደገና እዬሰፋ እንደሚሄድ ነው።አሁን ከተደረሰበት የትግል ከፍታ ላይ የሚገኝ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ካለውጤት ሊመለስና ሊበተን ይችላል ብለን አናስብም።አሁን ከተደረሰበት ከፍታ ላይ ለመድረስ የብዙ ዜጎች ህይወት ተከፍሎበታል።ለድል ለመብቃት ከተደጋጋሚ ውድቀቶቹ ተምሮ አሁን የሚታዩ አነስተኛ ድክመቶችን ማሶገድ ይገባል።ከድክመቶቹ ዋናው በተቃዋሚው ጎራ የሚታዬው በአንድ ድርጅታዊ ሰንሰለት አለመተሳሰሩና በአንድ ማእከላዊ አመራር ስር አለመመራቱ ነው።ይህ ክፍተት ከተደፈነ ለዘላቂው ሕዝባዊ ድል ማረጋገጫና ዋስትና ነው።የአጥፊው ቡድንም መግቢያ ቀዳዳ የሚሆነው ይህ ክፍተት መኖሩ ነው።በጎጥ፣ በከባቢ ልጅነት ፣በእምነት በጥቅማጥቅም እዬሸነሸነ ለመበታተን ለሚያደርገው ሙከራ እጅ ሳይሰጡ ጠንክሮ መቆም የጀግኖች ሙያ ነው። ጥቂቶች ለጊዜው ለጥቅም ቢማረኩ የኋላ ኋላ መዘዙ አይጣል ነው።የአብይ አህመድ "የሚፈልጉትን እያሳዬህ ወደምትፈልገው ንዳቸው፣ውሰዳቸው፤ቀጥለህም በሬ ሆይ ሳሩን አይተህ ገደሉን የሚለውን ተርትባቸው "የሚለው ፍልስፍናም የዚሁ የሰጥቶ ወይም አታሎ የማጥቃቱ ህሳቤ መነሻ ነው።ትናንትና ጀግናና ባለውለታ ብሎ አንገታቸው ላይ መዳሊያ ያጠለቀላቸውን ፋኖዎች ዛሬ እጃቸው ላይ ሰንሰለት ሲያስገባባቸው ማዬቱ ለአባባሉ ማረጋገጫ ነው።

አብይ አህመድ ትናንትና አብረውት የተሰለፉትን ሳይቀር አሳዷቸዋል፣ እያሳደዳቸውም ነው።እነለማ መገርሳና የመሳሰሉትን የዓላማ አጋሮቹን ለአጭር ጊዜም ቢሆን ፊት ነስቶ ገሸሽ አድርጓቸው ነበር አሁን ግን እሱም ሆነ ሌሎቹ ከያሉበት እንደጅብ ተጠራርተው እያሴሩ ለመሆናቸው ፍንጭ ወጥቷል። ዛሬ ያልተያዘው አድርባይና አጨብጫቢም ነገ መቀመቅ ላለመግባቱ ዋስትና የለውም።መታፈር በከንፈር

እንዲሉ ከሕዝብ ጋር ቢሰለፉ ይመረጣል።በትርፍራፊ ጥቅም መንግሥትን ለማወደስ የሚጮሁትን ጩኸት ለሕዝብ ብሶት መግለጫ ቢያውሉት ሌላው ቢቀር ለህሊናቸው እርካታና ደስታ ይሰጣቸዋል። ከሳሰኞች ነጻ የሆነች፣ሰላምና ዴሞክራሲ የሰፈነባት ኢትዮጵያም መኖር ለበለጠና ለተሻለ ኑሮ እንደሚያበቃቸው ሊረዱት ይገባል።ለአምባገነኖች ማደር ማለት በአጥንት እዬተታለለ ጅራቱን ቆልፎ የሚጮህ ውሻ መሆን ማለት ነው።

እነዚሁ ከእውቀት ጋር የተጣሉ ሆድ አደሮች በተሰለፉበት የዩቲዩብ ጫጫታ በሰሞኑ ያደረጉት የደደቦች ሆይሆይታ በሌላው ቀርቶ በሚደግፉት በአብይ መንግሥት በጠረባ የተመቱበትን አጋጣሚ ታዝበናል። አብይ አህመድ በዓለም ካሉ አንድ መቶ ተጽእኖ ፈጣሪዎች አንዱ ነው የሚለውን አባባል በቅጡ ሳይረዱ የኖቤል ሽልማት ዳግም ያገኘ ያህል ሲቦርቁ ታዝበናል።ተጽእኖ ፈጣሪ ማለት በበጎና በመጥፎ ተግባር መታወቅን የሚያመለክት እንጂ በመልካም ሥራ ብቻ የሚወደሱበት አገላለጽ አይደለም።ታዲያ በዚህ የተጽእኖ ፈጣሪነት ከሚታወቁት ለሰላምና ለሰብአዊ መብት የሠሩ እንዳሉ ሁሉ ዓለማችንን ያመሱ፣በሰብአዊ መብት ጥሰትና በወንጀል የሚታወቁ ችግር ፈጣሪዎችንም እንደሚያካትት መረዳት ተገቢ ነው።ተጽእኖ ማለትም ትኩረት የሳቡ ማለት ነው።ትኩረት ለመሳብም በበጎ ወይም በመጥፎ ሥራ መታወቅን ይጠይቃል።ይህንን ያልተረዱ ድንፋፍ እበላ ባዬች ግን አብይን ከበጎ አድራጊዎች ተርታ አስገብተው ከበሮ እዬመቱ ደልቀዋል።አሁን ላይ ግን የሚደግፉት መንግሥት ሳይቀር አባባሉን ተረድቶ ሲቃወም ነጭ ላብ አስምጧቸዋል።አብይ አህመድና የሚመራው ቡድን ዜጎችን በጎሳ ማንነታቸውና በሃይማኖት ለያይቶ የሚያዋጋ፣ የሚጨፈጭፍ፣የሃገርን ሃብትና ንብረት የሚያወድም፣ ጸረ ሰላምና ጸረ አንድነት ፣ጸረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሆነ፣ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብት ጠንክ ፣ውሸታምና አጭበርባሪ፣እራስ ወዳድ አምባ ገነን መሆኑ በግልጽ እዬታዬ መጥቷል።ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት እንዲያገኝ አድርጎታል።ለዚያም ነው በዓለማችን ተጽእኖ ወይም ችግር ፈጣሪ ተብሎ የተሰዬመው።ችግር ፈጣሪነቱንም በሚከተለው መስመር ላይ የሰፈረው በሚገባ ይገልጸዋል።

የአብይ አህመድ የኦሮሙማው ቡድን በአማራው ላይ የከፈተው ጦርነት ማጠንጠኛው በምዕራቡ አስገዳጅነትና ምክር ብሎም የገንዘብ ድለላ ከወያኔ ጋር እርቅ አውርዶ የወልቃይትንና የራያን መሬት አሳልፎ ለመስጠት እንቅፋት የሆነበትን ሃይል ለማሶገድ ያደረገው ዘመቻ መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ፤ የእኛም ግንዛቤ ከዚህ አይለይም።መጀመሪያ ላይ ከባቢዎቹን ከጎንደርና ከወሎ ነጥሎ በካርታ የማስቀመጡ የመፈተሻ ዘዴ በሕዝብ ተቃወሞ ሲከሽፍበት ወደለዬለት ጦርነት ገብቶ በጉልበት ነጥቆ ለማስረከብ የተደረገ ስምምነት ውጤት ነው።በኦህዴድና በወያኔ የጦር መሪዎች መካከል በኬንያና በሲችሊስ በተደረጉት የሸሽጎሽ ስምምነቶች መሠረት በውድ (በሕዝበ ውሳኔ)ሽፋን ቦታዎቹን አሳልፎ ለመስጠት መንገዱን ለመጥረግ ወያኔ ከሰሜን፣ኦሮሙማው ከደቡብና ምዕራብ በኩል የአማራውን መኖሪያ ክፍላተሃገር ሸዋን፣ ወሎን፣ጎጃምንና ጎንደርን በመክበብ ለዳግም ውድመት ያደረጉት ስምምነት ነው።መሬቶቹን የመስጠቱ ሃሳብ ሊተገበር የሚችለው የከባቢውን ነባር ኑዋሪ የሆነውን አማራውን ሲያንበረክኩ ብቻ እንደሆነ ስለተረዱት የመጨረሻ ሙከራቸውን ለማካሄድ ወስነው ተሰማርተዋል። ምስጢሩ የገባው አማራም የሞት የሽረት ትግል እያደረገ ይገኛል።በዚህ ዓይን ባወጣ ጭካኔና ወረራ ቁጥራቸው ያልታወቀ ሲሞቱ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ንጹሃን ታስረዋል። በአንጻሩም እስር ቤት ከሚገባው ይልቅ ጫካ የሚገባው በዝቷል።ብዙዎቹንም ለትግል ቀስቅሷቸዋል።በዚህ ወሳኝ ወቅት ለአገሩ አንድነት፣ለሰብአዊ ክብርና መብቱ የሚቆረቆር ዜጋ ሁሉ የትግሉ አካል በመሆን የሚያስፈልገውን ሁሉ እንዲያበረክት ጥሪ እናደርጋለን።ሁሉም በቃኝ ብሎ በአንድነት ሊቆም ይገባል።

የተረኛው የኦሮሙማው ቡድን አሁንም በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ላይ የሚያደርገው እብሪትና ከተማዋን የመዋጥ የመንደርደሪያ እርምጃ የከተማዋን ነዋሪ ሕዝብ አስቆጥቷል።ይህ ቁጣ ለሕዝባዊ

አመጽ እርሾ እንደሚሆን ብዞዎች ይናገራሉ፤የእኛም ግምት ከዚያ አይርቅም።ይህንን ስንል አገራችን ወደለዬለት ትርምስና ቀውስ እንድትገባ ፍላጎት ኖሮን ሳይሆን ለሕዝባዊ ሥርዓት ለውጥ ሕዝባዊ ትግል ማስፈለጉን በማመን ነው።የየካቲት 1966ቱን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ዋቢ በማድረግ የደረስንበት ድምዳሜ ነው።ለውጥ መምጣቱም አይቀሬ ነው።ብዙ መስዋእት የማይከፈልበትን ዘዴ መከተል ያስፈልጋል እንጂ ለውጡን ለማስቆም መሞከር የሰፈነውን ጎሰኛና ተረኛ ብሎም አገር አፍራሽ ስርዓት እንዲቀጥል ማድረግ ነው።በትግሉ ከሚደርሰው ጉዳት የበለጠ በጎሰኞቹ ስርዓት የደረሰውና የሚደርሰው ጉዳት ይበልጣል።

አገር በዚህ የቀውስ አውሎ ንፋስ እዬተናወጠች አብይ አህመድ የጫካ ላይ መዝናናቱን ቀጥሎበታል። ከዚያም አልፎ ተርፎ እንደ ሰላማዊ አገር መሪ በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች እዬተሽከረከረ ጊዜውን ያሳልፋል።በተደጋጋሚ እንደታዬው በአገሪቱና በሕዝቡ ላይ የሚወሰድ ከባድ እርምጃ ካለ አብይ አህመድ  እራሱን ነጻ ለማድረግ የሚዘጋጅበት ማምለጫ ዘዴ ለመሆኑ ያለፉ ብዙ ተመሳሳይ ማስረጃዎች አሉ።ይህ ዘዴ ፣በብልጣብልጥነት የሚበልጠኝ የለም፣እያታለልኩ እኖራለሁ ከሚል ግብዝነት የመነጨ ጅልነት ነው።

የብልጣ ብልጥ ፖለቲካ በአብይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም።ሌላው ብልጣብልጥ የኦሮሙማው ጸረ ኢትዮጵያ የሆነው ጁዋር ሙሃመድም ከሰሞኑ ለአገር አንድነት የቆመ፣ብጹእና የሰላም አባት መስሎ ብቅ ብሏል፣በአንድ የሚድያ ስርጭት ላይ ቀርቦ በሰጠው ማብራሪያ ጭራሽ የጦርነት ተቃዋሚና ለሰላምና ለሰብአዊ መብት  የቆምኩ ነኝ ሲል ተደምጧል። “ቀና ቢል በቆንጨራ አንገቱን እንቀነጥሰዋለን” ያለውን ከብዙዎቹ የድንፋታና የቅስቀሳ መልእክቶቹ ውስጥ መዘን በማውጣት ይሉሽን ባልሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ ወይም ጅብ ከማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ የሚሉትን ምሳሌ በመድገም  እኛም ሞኝህን ፈልግ እንላለን።ይህች ጨዋታ በሌሎቹ ምክርና ድጋፍ የተቃኘች የፖለቲካ ሙዚቃ እንጂ እውነትስ ጁዋር አምኖበት በጽናት የሚቆምለት እንዳልሆነ ሁሉም ያውቀዋል።ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ ማለቱ በሚገባ ይገልጸዋል ብለን እንገምታለን።ከወር በፊት በአማራው ላይ የዘመቻ እርምጃ እንዲወሰድበት መግለጫ ያወጣውን አፌኮ የተባለውን ድርጅት የሚመራው ጁዋር ሞሃመድ በፖለቲካ አክሮባት ተገልብጦ አባ ሰላማ ልሁን ሲል መስማቱ የሚያስቅ ቢሆንም ሰይጣንም ተለውጦ መለአክ ነኝ ብሎ ሊመጣ ይችላል የሚል የሞኝ ተስፋን ያስተናግዳል።ሰሚውን ሕዝብም የማስታወስ ችሎታ እንደሌለው የሚነዳ መንጋ አድርጎ የመቁጠር ድፍረት ነው።የአብይ አህመድ የሚፈልጉትን እያሳዬህ ----የምትለዋ ጨዋታ በጁዋር በኩል የሚፈልጉትን እዬተናገርክ ወደ ፈለክበት ውሰዳቸው ወይም የምትፈልገውን ውሰድ ከሚለው ምንጭ የተቀዳች ማሳሳቻ መርዝ ነች።በለውጥ ስም የስርዓቱ ተቀያሪ ጎማ ለመሆን በአሜሪካ ጋራጅ ውስጥ ንፋስ የሚሰበስቡ ጎሰኞችና የቀኝ አክራሪዎች መኖራቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ብልህ ሰው ደጋግሞ ግም ውሃ ውስጥ አይነከርም፣ ስለሆነም ጁዋር ሞሃመድና ተመሳሳይ የጎሳ ፖለቲካ አራማጅ ፖለቲከኞች የዬትኛውም አገር ድጋፍ ቢኖራቸው በአገራችን  የፖለቲካ ህይወት ቦታ እንደማይኖራቸው መግለጽ ተገቢ ነው። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ለመሳተፍ ኢትዮጵያዊ መሆን፣ ለኢትዮጵያኖች ፍቅርንና ክብርን ማሳዬትና ለኢትዮጵያ አገራዊ አንድነትና ጥቅም መቆምን ይጠይቃል! ለአገራዊ ቀውሱ ምክንያት የሆነውን የጎሳ ፖለቲካና ክልል የተባለ አጥር እንዲሁም ሕገ መንግሥት መወገድ እንዳለበት አምኖ መቀበልና ለዚያም መሥራት ይጠበቅባቸዋ።

ጁዋር ሙሃመድና መሰሎቹ ከተነከሩበት ጸረ ሕዝብና ጸረ ኢትዮጵያ አቋማቸው ተጸጽተው ለመታረም ዝግጁ ከሆኑ በቅድሚያ የሠሩትን ወንጀል በዝርዝር አምነው መቀበልና ሕዝቡንም ይቅርታ መጠዬቅ ይኖርባቸዋል።ከዚያ በኋላ በፍትሕ ሚዛን ላይ ተቀምጠው ጥፋታቸውን ማመናቸው የቅጣት

ማስተካከያ ቦነስ ተደርጎላቸው ተገቢው ውሳኔ ሊሰጣቸው ይገባል።ይህ የፍትሕን አሠራር መኖር ከማረጋገጡም በላይ ለሕብረተሰቡም ትምህርት ይሠጣል።ሌላም ወንጀለኛ እንዳይፈጠር ይከላከላል። ወንጀለኛ ሳይቀጣ ይኑር ማለት ሌላ ወንጀለኛ እንዲኖር ማበረታታት ይሆናል።

እኛም ፋኖ ነን፤ፋኖን ማሳደድ ይቁም!

ሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘላለም ትኑር!!!